# ግሼን ማርያም

(ዲ.ን ዳንኤል ክብረት)

ግሼን ማርያም በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት አምባሰል የምትገኝ ደብር ናት:: የአምባዋ መግቢያ በር አንድ ብቻ ሲሆን ዙሪያዋን በገደል የተከበበች ቅድስት ሥፍራ ናት:: በዚህች ታሪካዊት ሥፍራ ላይ ዐጼ ካሌብ ወደ ሀገረ ናግራን ዘምተው የክርስትና ጠላት የሆነውን ንጉሥ ፊንሐስን ድል አድርገው ሲመለሱ ታቦተ እግዚአብሔር አብን ወደ ኢትዮጵያ ይዘው መጥተው፣ በግሼን አምባ ላይ ቤተ መቅደስ ሠርተው፣ ቀዳሽና አወዳሽ መድበው ደብረዋታል (ደብር አድርገዋታል)::

ከዚያም በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ንጉሥ ላሊበላ የግሼንን አምባ ለማየት ሄደው ቦታውን ስለወደዱት ቤተ መቅደስ መሥረት ቢጀምሩ « ዚህ ቦታ ላይ (ቤተ መቅደስ) የምትሠራው አንተ ሳትሆን ዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ ነው» ተብሎ በሕልም ስለተነገረቸው ያሰቡትን ትተው ወደ ቦታቸው ተመልሰዋል እየተባለ በደብሩ ይተረካል::

በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ አባታቸው ዐጼ ዳዊት ያመጡትን የክርስቶስን ግማደ መስቀል «አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል- መስቀሌን በመስቀልያ (ሥፍራ) አኑር» የሚለውን ራእይ በማየታቸው በዚህ አምባ ላይ እንዳስቀመጡት በደብሩ ብቻ የሚገኘው **መጽሐፈ ጤፉት** ይናገራል:: ብዙ ርስትና ጉልትም ሰጥተው ደብሩን ጠግነውታል::

ግራኝ አህመድ የካቲት 22 ቀን 1532 ዓ.ም ወደ ግሼን አምባ መጣ:: በዚያ የነበሩ የልዑላኑ ልጆችና ሕዝቡ በድንጋይ ናዳ ብዙውን ሠራዊቱን ከጨረሱበት በኋላ አምባውን ሰብሮ በመግባት ልዑላኑን ፈጅቶ ከዐጼ ይኩኖ አምላክ መን ጀበሮ የተከማቸውን ሀብት (የወርቅ ዘውዱን፣ የወርቅ ጽዋዑን፣ የወርቅ ጻሕሉን፣ ግልገል ወርቁን፣ የወርቅ ጌጣጌጡን፣ የሐር ልብሳ ልብሱን፣ መጻሕፍቱን) ሁሉ ዘረፈ:: የግራኝ ታሪክ ፀሐፊ እንደሚለው «የመዝገቡን ልክ ከአላህ በቀር የሚያውቀው አልነበረም:: በዚያን ጊዜ ወርቅ እንደ ድንጋይ ረክሶ ነበር::»

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከጥፋት ይጠብቅልን:: አሜን::
ወስብሐት ለእግዚአብሔር